አንተስ እስከመቼ ደረስ ነው የፋሽስቶችና የባንዶች መሣርያ በመሆን የጭቁኖችን ልጆች፣ ሳብ አደሮችና አርሶ አደር ወዳጆችህን እያሰርክ፣እያሰቃየህና እየገደልክ አሳፋሪ ውድቀትህን የምትጠብቀው? የለም ከእንግዲህ ይበቃሀል ከጭቁኖች ጋር ተሰለፍ:: በጠላት ላይ ተነሳ:: ከተባበርክ ሰፊው ሕዝብ ከጎንህ አለና ሀይል አለህ:: አታመንታ:: የየካቲትን ወኔህን አሁንም መልሰው! ዛሬም ከምዝብሮች ጋር እንደያን ጊዜህ ተነስ!

ከላብ አደሮች ጋር ለአርነት በማለት
ከደሀ አርሶ አደር ጋር ለአርነት በማለት
ከተራማጆች ጋር ለአርነት በማለት
ከበጪራት ጋር ለአርነት በማለት
ከታጋይ ወጣት ጋር ለአርነት በማለት
የተበተበውን የግፉን ሰንሰለት
ሲራውን ደባውን ተንኮሉን ለመስበር
ደምህ የጭቁን ደም አጥንትህ የምዝበር
ጭቁኑ ወታደር ከህዝቡ ጋር አብር !!

ጭቁን ወታደር የግራዚያኒ ሥልጣን ለማደላደል በያለበት አያለቅም
ጭቁን ወታደር የባንዶች መሳርያ በመሆን ልጆችን አያርድም
የየካቲት ጭቁን ከማለትና ልጆችን በማሰረሽን በቁር የተረፈው የለም
ጭቁን ወታደር ሰፊው ህዝብ ከጎንህ ቆሟል
ጭቁን ወታደር በፕሮፓጋንዳ አይታለልም
በየበረሃው ያለኸው ጭቁን ከታጋይ ሀይሎች ጋር ተቀላቀል
የጭቁን ወታደሮችና የጭቁን ህዝቦች ትግል ያቸንፋል !!
ኢ.ህ.አ.ፓ. ከህዝቦች ጋር ዴል ይመታል !

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን !!

በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ዲ.ሲ ቻፕተር/ የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን አባል/ እንደገና ታይፕ ተደርጎ የተበተነ::